# መጤና ተዛማች እንጨታማ ዕጽዋት በምስራቅ አፍሪቃ:-

## በሥነ-ምህዳርና በሕብረተሰቡ የዕለት-ከዕለት ኑሮ ላይ የሚያደርስቱን ተጽዕኖ ማጥናትና መግታት:

http://www.woodyweeds.org/

## የመጤና ተዛማች ዕጽዋትን ተጽዕኖ በመቋቋም ዘላቂ የመሬት አጠቃቀምን ማጎልበት ::



ፕሮሶፒስ ጁሊፍሎራ (በአካባቢው አጠራር ደርጊ ሃራ - ወይም የወያኔ ዛፍ) በ1970ዎቹ ለተለያዩ ጥቅሞች ታስቦ ወደ ምስራቅ አፍሪካም ሆነ ወደ ሀገራችን እንደገባ ይነገራል፡፡ ከእነዚህም ጥቅሞች መካከል በርሀማነትን ለመከላከል፣ ለማገዶ እንጨት፣ ለአጥርና: ለከሰል አገልግሎቶች እየዋለ ይገኛል፡፡



*የእኔ የምርምር ዉጤት የተለያዩ ባለድርሻ አካላት - ማለትም ሕግ-አዉጪዎች፣ ተመራማሪዎች፣ የአካባቢዉ ነዋሪዎች እንዲሁም የልማት ጣቢያ ሠራተኞች እንደ አስፈላጊነቱ ሊጠቀሙበት የሚችሉት ሥራ እንደሚሆን ይጠበቃል፡*

*(ኃይሉ ሽፈራዉ ደስታ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲና በውኃና መሬት ሀብት ማዕከል የዶክትሬት ዲግሪ ተመራማሪ)*



በአሁኑ ሰዓት ፕሮሶፒስ በአፋር ክልል በተለይ በደቡባዊ አፋር ከፍተኛ ተêዕኖ እያደረሰ ይገኛል፡፡ የግጦሽ ጥራትን፣ እጥረትንና የውሃ እጥረትን በመፍጠር የብዝሃ-ህይዎት ስብጥርን በመቀነስ እንዲሁም የማሳ ስራን ለተጨማሪ ወጪ በመዳረግ ከፍተኛ ጉዳትን እያስከተለ ይገኛል፡፡



በዚህ ፕሮጀክት አማከኝነት በመስራቅ አፍረቃ አሁን ያለበትን የስርጭት ስፋትና ለወደፊት ምን ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችላል የሚለዉን በካርታ እያዘጋጀን ሲሆን፤ በሥነ-ምህዳር እና በአጠቃላይ ኢኮኖሚዉ ላይ ሊያደርስ የሚችለዉን ተፅዕኖም እናጠናለን፡፡ ይህም ሽፋኑ ምን ደረጃ ሲደርስ ነው ጉዳቱ ከጥቅሙ የሚያመዝነው የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ጥናት ይሆናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የእንስሳትና ሰው እንቅስቃሴ በፕሮሶፒስ ሥራጭት ላይ ምን ጉልህ አስተዋፆ አላቸዉ በሚለዉ ላይም የዳሰሳ ጥናት እንዲሁም የፕሮሶፒስ ዉሃ አጠቃቀም በእንስሳተ መኖ፡ በእንስሳት ርባታ እና በብዝሀ-ሕይወት ላይ የሚኖረዉን ተፅዕኖ እናጠናለን፡፡





ስለዚህ ይህ ፕሮጀክት የአካባቢውን ህብረተሰብ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፕሮሶፒስን ለመቆጣጠር የሚያደረጉትን ጥረት ለማገዝ፣ ጉዳቱን ለመቀነስና ጥቅሙን ለማሳደግ ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን ለዚህም ይረዳ ዘንድ የሰርቶ ማሳያ ጣቢያዎችን በማዘጋጀት የፕሮሶፒስ መቆጣጠሪያ ዘዴን የማገገሚያ ስልቶችን ሰርቶ ማሳያ የሚሆኑ ቦታዎችን አዘጋጅቶ ለሚመለከተዉ ሁሉ ያስተዋዉቃል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ ዶ/ር ጠና አላምረውን - በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የውኃና መሬት ኃብት ማዕከል ስ.ቁ. +251 922 470 113 ወይም ኢሜል: tena.a@wlrc-eth.org መጠየቅ ይቻላላል፡፡

Water & Land Resource Centre
Swiss Programme for Research on Global Issues for Development
Schweizerische Eidgenossenschaft
Confédération suisse
Confederazione Svizzera
Confederaziun svizra
Swiss Agency for Development and Cooperation SDC
FNSNF
Swiss National Science Foundation